# አገር እንዴት ሰነበተች?

አገር እንዴት ሰነበተች እስኪ ልጠይቃት

ሰላም ጤና ነች ወይ ከፋትስ ደስ አላት።

ማነው ከልጆቿ በጎ ሚመኝላት፣

በሰላም እንድትኖር አገር የሁሉም ናት።

በነዚህ ስንኞች ከሃምሳ ዓመት በፊት የቀዳማዊ ሃይለሥላሤ፣የአሁኑ ብሔራዊ ትያትር ባለሙያ ፣ በቴሌቪዥን የሕጻናት ክፍለጊዜ አቅራቢ የነበሩት አባባ ተስፋዬ ወይም አቶ ተስፋዬ ሳህሉ በሙዚቃ ታጅበው ዓለም እንዴት ሰነበተች?በሚለው ጨዋታቸው ያካተቱት ስንኝ ነበር።እኛም የሳቸውን መልእክት ተውሰን ዓለም በሚለው ፋንታ አገር እንዴት ሰነበተች በማለት ተጠቅመንበታል።ያ ትውልድ ከአገሩ አልፎ ለዓለም የሚጨነቅ እንደነበር ማሳያ ነው።የዛም ዘመን መሪዎች ከራሳቸው አገር አልፈው ለአፍሪካና ብሎም ለጭቁን የዓለም ሕዝብ የሚጨነቁና የሚሠሩ ነበሩ።የአፍሪካ አንድነት ምሥረታና የገለልተኛ አገሮች ህብረት እንቅስቃሴ የነዚያ ማሳያ አሻራዎች ናቸው።ምንም እንኳን እንደ ታሰበው ለመዳዝ እንቅፋቱ ቢበዛም፣የገለልተኛ አገሮችም ስብስብ ቢፈርስም የአፍሪካ አንድነት ድርጅት ግን እዬተንገዳገደም ቢሆን እስከ አሁን ድረስ ሊዘልቅ ችሏል።የነገው እጣፈንታው በአዲሱ ትውልድ ትከሻ ላይ ያረፈ ነው።ለነጮቹ ደባና ሴራ ከተንበረከከ፣ እንደተባበሩት መንግሥታት ድርጅት የከበርቴ አገሮች መንኮራኩር ከሆነ እንኳንስ ሙሉ አፍሪካ ቀርቶ አንድም የአፍሪካ አገር ነጻ ሆኖ አይኖርም።

ወደ ዋናው እርዕሳችን ስንመለስ የዛሬውም ዝግጅታችን እንዳለፉት ተከታታይ ቀንብሮቻችን ባለፉት ቀናት አገራችን ኢትዮጵያ ያለፈችበትን ጉዞ የሚዳስስ ይሆናል። ደጋግመን እንደገለጽነው በአገራችን ውስጥ በፖለቲካ፣በኤኮኖሚና በማህበረሰብ እንቅስቃሴ ዙሪያ የሚታዬው ክስተት ከመጥፎ ወደ ደህናና የተሻለ አቅጣጫ ሳይሆን ወደከፋና የባሰ አቅጣጫ የተዘፈቀ ሆኗል።

ከ 15 ወራት በፊት በሥልጣን እብዶች በህወሃት መራሹ የትግራይ አውዳሚ ሃይልና በተረኛው የኦሮሙማው ኦነግ መራሹ አውዳሚ ሃይል መካከል የተነሳው የሥልጣን ጦርነት ብዙ ውድመት፣የሕዝብ ሞትና መፈናቀል አድርሶ አገራችንን ለበለጠ ድህነትና የጠላቶች መሳቂያ መሳለቂያ አድርጓታል። በሕዝቡ እርብርቦሽና መስዋእትነት የወያኔና ኦነግ ወረራና ውድመት ጋብ አለ ሲባል እንደገና አገርሽቶበት ወያኔ ጠላቴ ነው በሚለው በአማራውና መፈናፈኛ በነፈገው በአፋሩ ማህበረሰብ ላይ የጥቃት እርምጃውን ለመቀጠል እንዲያንሰራራ በመንግሥት ነኝ ባዩ ታግዞ ለዳግመኛ ውድመት ተሰልፎ ቦታዎችን ተቆጣጥሮ ወደ ፊት እዬገፋ በመሄድ ላይ ነው።ይህ ሁሉ ሲሆን የሥልጣን እንጂ የዓላማ

ልዩነት የሌለው በሥልጣን ላይ የተቀመጠው የኦሮሙማ/ኦነግ መራሹ ቡድን የሚቆጣጠረውን የመከላከያ ሃይል በካምፕ ውስጥ አጉሮ እዬቀለበ የሚፈጸመውን እልቂት እንደ ጋራ ድል በመቁጠር አያገባኝም በሚል መልኩ ዝምታን መርጧል።ያም ብቻ አይደለም የራሱን የጦር ሹማምንት በመሾምና በመሸለም የሕዝቡን መስዋዕትነት በማራከስ ከድል ሽሚያ ውስጥ ገብቶ አላግጦበታል። የራሴ ነው በሚለው የኦሮሚያ ክልል የሚኖረውን ሌላ ጎሳ ተወላጅ በተለይም አማራውን በአረመኔ ተላላኪዎቹ እዬገደለና እያፈናቀለ ቦታውን በማጽዳትና የልማት እንቅስቃሴውን በሌሎቹ  ክልሎች ኪሳራ እያስፋፋው ይገኛል።የሌላው አካባቢ በተለይም የአማራውና የአፋሩ ከነበሩበት ጭማቂ የዕድገት  ጭላንጭል ደረጃ ወደ ከሰላሳ ዓመት በፊት ወደነበሩበት ድህነት መልሶ ከቷቸዋል።

በኢትዮጵያዊነታቸው የሚያምኑትን የአማራውንና የአፋሩን  መኖሪያ መሬቶች ወሮና አሶርሮ ጦርነቱ አብቅቷል በሚል ትርክት የባዕዳን አገሮችን ለማስደሰትና የነፈጉትን እርዳታ ለማግኘት፣ሥልጣኑንም ለማስጠበቅ በአብይ አህመድ የሚመራው የብልጽግና(የብልግና ቢባል ይሻላል)መንግሥት ነኝ ባይ ቡድን ከሌሎቹ ብዙ ክህደቶች በላይ የሆነ ክህደት ፈጽሟል።የወንጀለኞቹ መፈታትም የዚያው ክህደት መንደርደሪያ መሆኑ በግልጽ ታይቷል። በዚህም ብቻ አላቆመም ከወያኔ ጥፋት ሃይሎች ጋር ለመደራደር ሽማግሌ በመላክና በመቀበል ላይ ተጠምዶ ይገኛል። ይህ የፖለቲካ ቁማር ለበለጠ ቀውስና የአገር መበታተን ይዳርግ እንደሆነ እንጂ ለተሻለ ሰላምና አንድነት አያበቃም።

የኦሮሙማው ስብስብ የአገሪቱ ፈላጭ ቆራጭ ሆኖ እንዲቆይ ለማድረግ በውስጡ ያለውን የሥልጣን ሽኩቻና አለመግባባት አሶግዶ ጠንክሮ ለመቆም ከዬቦታው ተሰባስቦ በሬ አርዶ መማማሉን ባለፈው ሰሞን ያዬነው ሃቅ ነው።የኦሮሙማው ስብስብ በታሪኩ ያላገኘውን የሥልጣን ብቸኛ ባለቤትነቱን አሳልፎ ላለመስጠት የማይቆፍረው ጉድጓድ፣ የማይገለብጠው ድንጋይ የለም። ሁሉም ነገር የኛና በእኛ መሆን አለበት በሚለው ቅዠትና ሌላውን የናቀ እብሪት ሊሳካ የሚችለው ሌላው ኢትዮጵያዊ  በተለይም አማራውና አፋሩ ከገባበት ሽለብታ ድባብ ውስጥ  ሳይነቃ ለጥቃት ምቹ ሆኖ እንዲኖር ማድረጉ ታምኖበት የማጥቃት እርብርቦሹ በስፋት ቀጥሏል።ይህ ሊሳካላቸው የሚችለው ግን ሃይሉንና ካላጠናከረና ወይም አሁን በዬቦታው የሚያደርገውን እምቢ ባይነት በውስጥ ችግርና መከፋፈል ከተዳከመና በተሸናፊነት ካቆመ ብቻ  ነው።ይህ እንዳይሆን ለኢትዮጵያ አንድነትና ለእኩልነት ብሎም ለፍትሕና ዴሞክራሲ የቆመው ወገን ደጋፊው ጠንክሮ መሥራት አለበት።

የአማራው ማህበረሰብ የሚያደርገውን ትግል በተቀናጀ መልክ መምራት እንዳለበት በተደጋጋሚ አሳስበናል ጥሪም አድርገናል።አሁንም ጥሪያችንን አናቆምም።መነሳሳቱ ተስፋ የሚሰጥ ሆኖ ሳለ አሁንም እንቅስቃሴው በተበታተነ መልኩ  እንደሆነ ይታያል።የአማራው ትግል እራሱን አድኖ ኢትዮጵያን ከመበታተን ማዳን ነው።ኢትዮጵያን ማዳን ማለትም

መላውን የኢትዮጵያ ሕዝብ ከጥፋትና ከውድመት፣ከባርነትና ከእጅ አዙር ቅኝ አገዛዝ ማዳን ማለት ነው።ስለሆነም በጠባብ አስተሳሰብ ላይ የተነደፈ የትግል ዓላማ የለውም። በዩቦታው ብቅ ብቅ ያሉትና በማለትም ላይ ያሉት ስብስቦች ወደ አንድ ግንባር መካተት ይኖርባቸዋል እንላለን።በአማራው ስም በልዩ ልዩ ስያሜ የሚንቀሳቀሱት ሁሉ በአንድ ጥላ ሥር ካልተሰለፉ ለጠላትና ለአወናባጆች የተመቼ ሁኔታ ይፈጥራሉ።

ስለሆነም የአማራ ፋኖ፣የአማራ ነጻ አውጭ ግንባር፣ሞረሽወገኔ፣የአማራ ሕዝብ እርዳታ አሰባሳቢ፣የፋኖ እርዳታ አሰባሳቢ፣የአማራ ማህበራት ጉባኤ፣ጋሻ፣አለን ---ወዘተ የሚሉት ሁሉ፣ ሌሎቹም በአንድ ድርጅታዊ መዋቅር ውስጥ ሊካተቱ ይገባል።ፋኖን በጎጥ ገመድ ለማሰር የሚሞክሩ አይጠፉምና ለነዚያ ዕድል እና መግቢያ በር እንዳያገኙ ማድረግ ለትግሉ ዘላቂ ዋስትና ነው።በተጨማሪም የፋኖ ትግል የሁሉም አገር ወዳድ ትግል ስለሆነ በአንድ የፖለቲካ ድርጅት መዳፍ ውስጥ እንዳይገባ መጠንቀቅ ጠቃሚ ነው።የፖለቲካ ድርጅት መንኮራኩር ከሆነ ለመበታተንና ለእርስ በርስ ግጭት ምክንያት ይሆናል።ፋኖ የፖለቲካ ሥልጣን ለመያዝ የተደራጀ አይደለም።አባላቱን ያሰባሰበው የጋራ የማንነትና አገራዊ ጥቅም ሲሆን ዓላማው ሲሳካለት ወደመጣበት የሚመለስ ስብስብ ነው።የፖለቲካ ድርጅቶች እንዳይጠቀሙበት ነጻነቱን ጠብቆ መንቀሳቀስ ይገባዋል።በአስፈላጊ የጋራ ዓላማ ላይ ከመተጋገዝ ባለፈ አንዱ በሌላው ውስጥ የመግባት ወይም አካል የመሆን አዝማሚያ ሊኖር አይገባም።የፖለቲካ ፓርቲ ለአንድ የተወሰነ የማህበረሰብ ክፍል ጥቅም የሚመሰረት፣ለሥልጣን የሚታገል ሲሆን ፋኖ ግን ሕዝባዊና የሁሉንም የጋራ ፍላጎት የሚያስከብር ስብስብ ነው።

ሌላው የሰሞኑ አነጋጋሪ ጉዳይ አብይ አህመድ ጋዜጠኞችንና ዲያስፖራ የተባለውን ከንቱ ስብስብ በግንቦት ሰባቱ በነአምን ዘለቀ መልማይነትና አጋፋሪነት በጽህፈት ቤቱ ሰብስቦ ማናገሩ ነው።በዚህ ስብሰባ ላይ የተወሰኑት ብቻ ተመርጠው የቀረቡ ሲሆን ለይምሰልም የፈለጉትን ጥያቄ እንዲያቀርቡ ተፈቅዶላቸው እንደነበር፣አብይ አህመድ ለተሰብሳቢዎቹ ከሕዝቡ የተለዩ ታማኞችና ምስጢር ጠባቂዎች እንደሆኑ በመግለጽ የሰሙትን ወደ ውጭ እንዳያወጡም አደራ ማለቱን የተሳታፊዎቹ ቃል አቀባዮችና ወኪሎች ተናግረዋል። በተጨማሪም ከስብሰባው በኋላ በሰሙት ማብራሪያ ደስተኞችና የረኩ መሆናቸውንም ገልጸዋል።ከተናገሩትም መሃል የማናውቀውና እስከዛሬ ስንቃወመው የነበረው ስህተት ሆኖ አገኝተነዋል፤ብዙ እንዳናወጣቸው ቃል ያስገቡንን ምስጢሮች ነግረውናል።የእስረኞቹ መፈታት፣የእኛ የዲያስፖራው አገር መግባት ብዙ ትሩፋቶች እንዳስገኙ ሳይደብቁ ነግረውናል።የኢሚሬትና የሌሎቹ አገራት ድጋፍና እርዳታ፣የአፍሪካ ጉባኤ እንዲካሄድ መፍቀዱ፣የራቁት የአውሮፓ አገሮችና የአሜሪካኖቹ መጣ መጣ ማለትና ተቃውሟቸውን ማላላታቸው የዲያስፖራው አገር መግባት ጋር የተያያዙ ውጤቶች መሆናቸውን ገልጸውልናል።የወልቃይት ጉዳይ በሚያስተማምን ደረጃ መልስ አግኝቷል፣ወያኔ ከአሁን በኋላ ለከባቢው አደጋ እንደማይሆን ለመረዳት ችለናል።ይህን የመሰለው መንግሥትና ተቃዋሚው ተቀራርቦ መሥራት አዲስና ይበል የሚባል የፖለቲካ ቅኝት ነው።እኛም

ከተቃወም ይልቅ ከመንግሥት ጋር ተቀራርቦ መሥራቱን አምነንበታል ብለዋል። የወያኔና የኦነግ ጥምር ወራሪ ሃይል በአማራውና በአፋሩ ሕዝብ ላይ ለዳግመኛ ጊዜ መሬቱን ተቆጣጥሮ ጥቃት ሲፈጽም የመንግሥት ችልታና ዝምታ አያሳስባቸውም፤እንደውም በድፍረት እዚህና እዚያ ያለ ትንሽ ግጭት ነው ለማለት ደፍረዋል።ቀደም ሲልም በአማራው ላይ ጀኖሳይድ አልተፈጸመም የሚል አቋም ነበራቸው። አገራችንንና ሕዝቡን ለዚህ መከራና ቀውስ የዳረገውን የጎሳ ፖለቲካና የሚመራበትን ሕገ መንግሥት በሚመለከት ላይ ግን ጥያቄ ማንሳታቸውንና መልስም መሰጠቱን አልገለጹም። ባያሳስባቸውና ባያነሱት እንጂ በዚህ ወሳኝ ጥያቄ ላይ የተባለ ቢኖር የመጀመሪያው ያደርጉት ነበር።የእስረኞቹንም መፈታት በጸጋ ተቀብለውታል።የወንጀለኞች መፈታትና የኦነጋውያን መሰባሰብ አያስጨንቃቸውም።የነሱ ጭንቀትና ሃሳብ መንግሥትን ተጠግቼ ምን ያህል ገንዘብ ወይም ካሬ ሜትር ቦታ አገኛለሁ የሚለው ጉጉት ነው።እነሱን ከሕዝቡ ነጥሎ ሚስጥረኛ ስላደረጋቸው፣የውጭ አገር ብድርና እርዳታ ከነሱ አገር መግባት ጋር የተያያዘ መሆኑን ስሰሙ የሙቀት መጠናቸው እዬጨመረ ከማጨብጨብ በዘለለ እንዴት ከሕዝቡ የተሰወረ ሚስጢር ይነገረናል?እኛ ያወቅነውን ሕዝቡ ሊያውቀው ይገባል ብለው አልጠዬቁም። ወትሮስ ቢሆን ከስድስት ዓመት በፊት አማራውን አግልሎ ከኦነግ ጋር ጥምረት የፈጠረው ግንቦት ሰባት ካዘጋጀው ስብሰባና ግንቦት ሰባት የተሳተፈበትን መንግሥት ከሚመራው ከአብይ አህመድ የሚሰጠውን ማብራሪያ አድንቆ ከመቀበል ሌላ ማን ደፍሮ ያጣጥላል?ከዚያ የተለዬ ለማድረግ የሞራል ብቃት የላቸውም። የሚቃወመውማ በቤተመንግሥት ለመብላትና ለመጠጣት ቀርቶ በከተማዋም እንደልቡ አይንቀሳቀስም።እንኳንስ በቤተመንግሥት ውስጥ በራሱ ወጭ በመለስተኛ ሆቴልም አዳራሽ ስብሰባ ለመካሄድ መብት የለውም። ታፍሶ ይታሰራል እንጂ በዝምታ አይታለፍም።ጋዜጠኛ ቢሰበሰብ ያው የመንግሥት አወዳሽ፣ዲያስፖራ ቢሰበሰብ ያው የመንግሥት አጨብጫቢና ግብር በሌው ብቻ ነው።እነዚሁ ጉደኞች በያሉበት አገር ተቃዋሚ መስለው ሰርገው በመግባት የተቃዋሚውን ትግል እንዲያኮላሹት ግዳጅ(ሚሽን) ተሰጥቷቸው መላካቸውን ከስብሰባው ዝግጅት ጀምሮ በድብቅ የወጣው ማስረጃና ማስጠንቀቂያ ያረጋግጣል። የሰጡትም አስተያዬት የዚያ አመላካች ነው።ስለሆነም በጋዜጠኛና በፖለቲካ ተንታኝነት ስምና ካባ ሊያዘናጉ የሚችሉ አድር ባዬችን በንቃት መከታተልና ፊት መንሳት ተገቢ ነው።አብዛኞቹን የሚኖሩበት አገር ነዋሪ በእኩይ ምግባራቸው ስለሚያውቃቸው ይሳካላቸዋል የሚል እምነት የለንም።ግን ዱሮም መስለው እዬገቡ ብዙ ጉዳት ማድረሳቸው ስለማይዘነጋ አሁንም ላለመዘናጋት ጥንቃቄ እንዲደረግና አካፋን አካፋ ብሎ ፊት መንሳት እንደሚያስፈልግ ልናስገነዝብ እንወዳለን።መርሳት የሌለባቸው ነገር በቤተመንግሥቱ ውስጥ ከአብይ ጋር በመከሩትና በተካፈሉት ሚስጥር ምክንያት በአገራችን ላይ ለሚደርሰው ችግር ተጠያቂ እንደሚሆኑ ነው።የበቃን(NO MORE) እንቅስቃሴን ለማኮላሸት ቃል መግባታቸውና ማድረጋቸው ኢትዮጵያን ብቻ ሳይሆን የዓለምን ጭቁን ሕዝብ በተለይም የአፍሪካን እንደካዱትና የምዕራባውያን የጥቅም ፈረሶች እንደሆኑ ሊያውቁት ይገባል።

መቼም በዬቀኑ የማይሰማ ጉድ የለም፣ፋኖን ለማጥፋት መንግሥት ወስኖ ሃይሉን በማሰማራት ላይ ይገኛል።የመንግሥት ካሮሳ ወይም አሽከር የሆነው ብአዴን የተባለውም እንኩቶ ስብስብ በፊት አውራሪነት ተሰልፏል፣የአማራው ክልል መሪ የነበረው የአሁኑ የደህንነት መረብ ተቋም ሃላፊ ጥሩነህ ተመስገን የሚመራው ተቋም መመሪያ አውጥቶ ለማስፈጸም ሽርጉድ እያለ ነው።ይህንን የኦሕዴድ ኦነግ ሴራ መንግሥታዊ ሽፋን በመስጠት ለአማራውና ለአፋሩ ህልውናና ለኢትዮጵያ አንድነት የሚፋለሙትን ጀግኖች አድኖ ለማጥፋት የሚደረገውን ሴራ ሁሉም ሊቃወመውና ሊያጋልጠው ይገባል።ይህ ሴራ የወያኔና የደጋፊዎቹ ምዕራባውያን ጭምር ነው።በአገር ላይ የተቃጣ ጥቃት ነው።

ተስፋ የሚሰጥ ወሬም እዬተሰማ ነው።የብልጽግና ተብዬው ኦሕዴድ-ኦነግ መራሹ ስብስብ በተረኞቹ ተንኮል ላይ ጥያቄ በማንሳት ሽኩቻ መከሰቱ ተሰምቷል።ብአዴን፣አፋር፣ሶማሌ፣ ሃረሪና ደቡብ የተባሉት የብልጽግና አባላት "የመንግሥት መንገድ ግራ አጋብቶናል"በማለት ሽኩቻና አለመግባባት ውስጥ መግባታቸው ይነገራል።ልዩነቱ ካደገና ከጠነከረ የብልጽግና ነገር ያበቃለታል ማለት ነው።ያ ደግሞ ለአገራችን ይዞት የሚመጣው ነገር ቀውሱን አባብሶት አገራዊ አደጋውን ያፋጥነዋል ብለን እንሰጋለን።ምንም እንኳን የብልጽግና በሥልጣኑ ላይ መቆዬት ለአገራችን አንድነት፣ሰላምና ዴሞክራሲ ይረዳል ባንልም ብልጽግና ሲፈርስ አገራችንን ይዟት እንዳይፈርስ አገር ወዳዱ እጅ ለእጅ ተያይዞ አገሩን ማዳን ይኖርበታል፤ያለው አማራጭና ብቸኛ ሃይል ፋኖ ስለሆነ ማጠናከርና ማገዝ የግድ ይላል።

በቀውስ ውስጥ የሚርመጠመጠው ብልጽግና በዲፕሎማሲ መስኩም እንዲሁ ትርምስ ላይ ነው።የሚያስጉትንና ሊጠቅማቸው ወይም ሊያርቃቸው የሚፈልጋቸውን ሰዎች ካለችሎታቸው፣ ካለሙያቸውና ካለፍላጎታቸው አምባሳደር አድርጓቸዋል።ከወራት በፊት አስፈላጊ አይደሉም፣ወጭም ይቀንሳል በማለት ከሰላሳ በላይ ኤምባሲዎችን መዝጋቱ የሚታወቅ ነው፤የአሁኑ የኤምባሲ ጋጋታ ለምን ጥቅም ይሆን?የኤኮኖሚው አቅም ስለፈቀደ?

የብሔራዊ ምክክር ኮሚሽንም ማቋቋሙ የሰሞንኛው ወሬ ነው።የሰዎቹ ስም ዝርዝር ቢገለጽም በማን እንደተመለመሉ፣ተጠሪነታቸው ለማን እንደሆነ፣የጋራ አቋማቸው ምን እንደሆነ፣እነማንን ለማማከር እንዳሰቡ፤ እነማን በምክክሩ ላይ እንደሚሳተፉ ፣ፓርላማው በአሸባሪነት የመደባቸው ሃይሎች ኦነግና ወያኔ ምን ቦታ እንደሚይዙ፣ለተመካካሪዎቹ የሚቀመጠው ቅድመሁኔታ ምን እንደሆነ፣ የተሰጠ ማብራሪያ የለም። የብልጽግና የውስጥ ሽኩቻ ወደ መጥፎ አቅጣጫ ካላመራ ውጤቱን የምናዬው ይሆናል።

በኤኮኖሚው ዙሪያ ባሳለፍነው ሰሞን ውድቀቱ ተባባሰ እንጂ አልተቀዬረም፣በዬቀኑ የዋጋ ግሽበቱ ይጨምራል፣ሰው በአቅሙ ሸምቶ የሚኖርበት አገር አልሆነም።የቤት ኪራዩ፣ የምግብ ዋጋው፣የሕክምናው ፣የመድሃኒቱ(ለዚያውም ከተገኘ)የሚመኙት እንጂ የሚያገኙት አልሆነም።ሁሉም ነገር ከአቅም በላይ ሆኗል። በሚሊዮኖች የሚቆጠር ሕዝብ አሁንም

የምግብ እርዳታ ያለህ እያለ ነው።እርዳታ ያላገኘው ብዙሃኑ ለሞት ተዳርጓል።ድርቅና ሰው ሰራሽ እርሃብ ከህወሃትና ከኦነግ አረመኔያዊ ጥቃት ጋር ተደራርበው የሕዝቡን ስቃይ አብዝተውታል።የሚያጣጥረው በሞተው የሚቀናበት ጊዜ ላይ ደርሰናል። ለባለጊዜዎቹ ግን የጎደለባቸው ነገር የለም።የቅብጠቱና የመዝናናቱ ነገር ገደብና ልክ የለውም።ከውጭ አገር ውድ አልባሳት መኪናዎችና ጌጣጌጦች አሁንም የባለጊዜዎቹ ዕለታዊ ወጭዎች ናቸው። የመዝናኛ ሆቴሎችና የፓርክ ግንባታዎች የመንግሥትን ትኩረት የሳቡና ቅድሚያ የሚሰጣቸው ናቸው።በመንግሥታዊ ተቋማት ግንባታና እድሳት ሰበብ የሚወጣው ወጭና ዘረፋው አይጣል ነው።አሁንም የቅደም ተከተሉ ነገር በዬትኛው ተቋም ሰበብ ልዝረፍ እንጂ የትኛው አስፈላጊ ነገር ይቋቋም አይደለም። የትኛው የልማትና የእርሻ ልማት ይሠራ፣እራብንና በሽታን እንዴት እንቋቋም ወይም እናሶግድ፣ችግረኞችን እንዴት እንታደግ፣ ዘላቂ ሰላምና የአገር አንድነት ብሎም ልዑላዊነት እንዴት ይከበር የሚለው አይደለም።የተለመደው መግለጫ ለዚህ እድሳት፣ለዚያ መናፈሻ ይህንን ያህል ቢሊዮን ወጣ የሚለው በመሆኑ የቢሊዮንን ትርጉም አሳጥቶታል።ዱሮ ሚሊዮን የሚለው ቁጥር እንኳን በሰው ስምነት ብቻ የሚታወቅ ነበር።አሁን ግን ዕድሜ ለነብክነቱ ይሁንና የማናውቃቸውን   የቁጥር ስሞች ለማወቅ ችለናል።በኢትዮጵያ ኤኮኖሚ ደረጃ ለአንድ መለስተኛ ሕንጻ መሥሪያ ወይም ማደሻ ከቢሊዮን በላይ ወጣ ሲባል ያገሪቱ ጠቅላላ ገቢ ስንት ቢሆን ነው የሚል ጥያቄ ይጭራል።ለነጉድ ጌጡ ግን ከባድ አይደለም።የብድርና የእርዳታ ያለህ የሚል መንግሥት መሆኑን ዘንግቶታል።የምርት ማሽቆልቆል ገሃድ በሆነበት አገር የብዙ ቢሊዮኖች ወጭ ሲሰማ ገንዘቡ ከዬት መጣ?ወይስ የሚታተምበት ወፍጮ ቤት አለ? ያሰኛል።በትጋት የሚሠራበት የኦሮሞ ክልል ግን በልዩ ልዩ ተቋማት ግንባታዎች እዬተምነሸነሸ መምጣቱ በግልጽ ይነገራል።የእነ አቶ እንደልቡ ፣የነማን አለብኝ ትእቢትና ድፍረት  መረን ለቋል።ሌላው ጋር ውድመት እነሱ ጋር ዓይን ያወጣ ዘረፋና  ልማት የሚካሄድበት የተረኝነት ሥርዓት መሆኑ በግልጽ ታይቷል።

ለጎረቤት አገራት የኤሌክትሪክ ሃይል ሽያጭ እንዳለም ይፋ ሆኗል። ገንዘቡ ግን ስንትና ዬት እንደሚገባ አይታወቅም።በአገሪቱና በሕዝቡ ስም የሚገኘው ብድርና እርዳታ የት እንደገባ መጠዬቅም ወንጀል ነው።ግለሰብ የሚያዝበት የግል ንብረት ሆኗል። የዬግድቡ ሥራ ገጠሩን በብርሃን ያጥለቀልቃል የተባለለት ተረትተረት ሆኖ የገጠሩ ሕዝብ አሁንም በጨለማ ውስጥ እዬዳከረ ነው። የሕዳሴውም እንዲሁ ለውጭ አገር የገንዘብ ግብአት እንጂ ለአገር ውስጥ አገልግሎት እንደማይውል ገና ካሁኑ የሽያጭ ውል እዬተፈረመ ነው። ከነዳጅ እጥረት ጋር በተያያዘም የመጓጓዣ ዋጋ አይጣል ያሰኛል።የአጋዴው የነዳጅ ምርት ለእንቁልልጮሽ የቀረበ ቀልድና ጨዋታ ሆኖ  ወሬውም አይነሳም፤ውሾን ያነሳ ውሾ ይሁን ተብሎ ጭጭ ምጭጭ ሆኗል።ቢወጣም የጎሰኝነቱ ስርዓት እስካለ ድረስ የግጭት ምክንያት ይሆናል እንጂ  ለጋራ ጥቅም መዋሉ ያጠራጥራል።

በማህበረሰቡ  በኩል የነበረው ተስፋ መቁረጥና ተቃውሞ በመጠናከር ላይ ነው።የተረኞቹ የኦነግ ቤተሰቦች የሚፈጽሙት በደልና ግፍ ብሎም ማን አለብኝነት የሕዝቡን ቁጣ

አባብሶታል።የጥምቀት በዓሉን ተከትሎ በተፈጸመው ድፍረት በጠፋው የሰው ሕይወት ምክንያት የኦርቶዶክስ ተዋህዶ አማኝ የሆኑትን የአማራ ተወላጆች ብቻ ሳይሆን የሌላውን ጎሳ ተወላጅ ኦርቶዶክሳውያንንና ለእኩልነት የቆሙ ሙስሊሞችን በአንድ ላይ በአንድ ሰንደቅ ዓላማ፣በነባሩ በአረንጓዴ፣ቢጫና ቀይ ስር እንዲሰለፉ አድርጓቸዋል።መንግሥት ከኦርቶዶክስ ተዋህዶ ላይ እጅህን አንሳ የሚለው ጥሪ ከያቅጣጫው እያስተጋባ ነው፤አንዱ የትግል አካል ሆኗል።።ነገም በሙስሊሙ አማኝ ላይ ሊደገም ስለሚችል መዘናጋት አይገባም።ይህንንና በጎሳ ማንነት የሚፈጸመውን በደል ለመቋቋምና እስከነአካቴው ለማሶገድ፣አገርንም ለመታደግ የዚህ አይነቱ የሕዝብ አብሮነትና መተጋገዝ ወሳኝ በመሆኑ ሊያድግና ይበልጥ ሊጠናከር ይገባዋል ፤ይህ ሕዝባዊ እንቅስቃሴ የጋራ ግንባሩ አካልም ተደርጎ ይወሰድ እንላለን።

የአንድነት ሃይሎች ግንባር ለኢትዮጵያ አንድነት ዋስትና ነው!

ኢትዮጵያ በልጆቿ አንድነት ተከብራና ታፍራ ለዘለዓለም ትኑር!!!

በስዊድን የኢትዮጵያ አንድነት ራዲዮ የስነጽሑፍ ክፍል